## ለቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ የሚፈቀዱ የካፒታል ዕቃዎችን ለመወሰን የወጣ የኢንቨስትመንት ቦርድ መመሪያ ቁጥር 39/2013

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት በአገሪቱ ኢንቨስትመንትን ማበረታታት፣ ለማስተባበርና ለማስፋፋት አዋጅ ቁጥር 769/2004ን/እንደተሻሻለ እና ይህንኑ አዋጅ ለማስፈጸም ስለኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችና ለአገር ወስጥ ባለሀብቶች ስለተከለሉ የስራ ማስኮች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 270/2005ን/እንደተሻሻለ/ ያወጣ በመሆኑ፤

በዚሁ ደንብ ለቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ማለትም የኮከብ ደረጃ ላላቸው ሆቴሎች

የሪሶርት ሆቴልን ጨምሮ/፣ሞቴሎች፣ሎጆችና ሬስቶራንቶች የካፒታል ዕቃዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ የሚፈቀድ በመሆኑ፣

እንደ ፕሮጀክቱ ስፋት እየታየ ለቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የካፒታል ዕቃዎችን ዓይነትና ብዛት መወሰን በማስፈለጉ፣

የኢንቨስትመንት ቦርድ በኢንቨስትመንት ዓዋጅ ቁጥር 769/2004 አንቀጽ 29 /4/ መሠረት ይህንን መመሪያ አወጥቷል፡፡

### አንቀጽ 1 አጭር
### ርዕስ

ይህ መመሪያ "ለቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ የሚፈቀዱ የካፒታል ዕቃዎችን ዓይነትና ብዛት ለመወሰን የወጣ የኢንቨስትመንት ቦርድ መመሪያ ቁጥር 38/2013 ዓ.ም» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### አንቀጽ 2
### ትርጓሜ

1. የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ወስጥ፡

   1.1 "የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት" ማለት ስለቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ደረጃ ምደባ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 173/2002 መሠረት ሆቴል፣ ሞቴል፣ሎጅ ወይም ሬስቶራንት ማለት ነው፡፡ ሆኖም በዚህ መመሪያ ፔንሲዮን እና ከባለአንድ ኮከብ ደረጃ በታች ያሉ ሆቴሎች፣ ሞቴሎች፣ሎጆች ወይም ሬስቶራንቶች አይሸፈኑም፡፡

   1.2 "ሆቴል" ፣"ሞቴል" ፣"ሎጅ" ፣"ሬስቶራንት" ስለቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ደረጃ ምደባ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር173/2002 መሠረት የተሰጣቸዉን ትርጓሜ ይይዛሉ፡፡

   1.3 "ሪሶርት ሆቴል" ማለት ለመዝናናት፣የዕረፍት ጊዜን ለማሳለፍ ወዘተ... ከከተማ ወጣ ብሎ በቱሪስት መዳረሻ ቦታዎች ወይም በመዝናኛ ስፍራዎች የሚቋቋም ዘመናዊ ሆቴል ነው፡፡

   1.4 "ዓዋጅ" ማለት የኢንቨስትመንት ዓዋጅ ቁጥር 769/2004 / እንደተሻሻለ ነው፡፡

1.5 "ደንብ" ማለት ስለኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችና ለአገር ወስጥ ባለሀብቶች ስለተከለሉ- የስራ ማስኮች የወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 270/2005 እንደተሻሻለ ነው፡፡

2. በዚህ መመሪያ ወስጥ ያሉ ሌሎች ቃላትና ሀረጎች በኢንቨስትመንት ዓዋጁና ደንቡ የተሰጣቸውን ትርጓሜ ይይዛሉ፡፡

## አንቀጽ3

## የካፒታል ዕቃዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲያስገቡ የሚፈቅድላቸው የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች

1. የኢንቨስትመንት ፈቃድ ያወጣ ባለሃብት አዲስ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪድርጅት ለማቋቋም ሲፈልግ ወይም ነባር የቱሪስት አገልግሎት ሰጪድርጅት በኢንቨስትመንት አዋጁ ላይ በተጠቀሰው ሁኔታ ማስፋፋት/ማሻሻል ሲፈልግ ወይም በአዋጁ ላይ ከተጠቀሰው ባነሰ ሁኔታ ኢንቨስትመንቱን ማስፋፋት/ማሻሻል ሲፈልግ በዚህ መመሪያ መሠረት ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልጉትን የካፒታል ዕቃዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ ይፈቀድለታል፡፡

2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ/1/ ድንጋጌ ቢኖርምየቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ለማቋቋም የፈለገ ባለሃብት የኢንቨስትመንት ፈቃድ አውጥቶፕሮጀክቱን ተግባራዊ በሚያደርግበት ወቅት እና የንግድ ሥራ ፈቃድ ካወጣ በኋላ ደግሞ ቢያንስ 200 ሺህ የአሜሪካን ዶላር ወይም በወቅቱ ምንዛሪ ተመጣጣኝ የኢትዮጵያ ብር ኢንቨስት ካደረገ እናቢያንስ50 ቋሚ ሠራተኛ የቀጠረ ከሆነ የንግድ ሥራ ፈቃድ ካወጣበት ቀን ጀምሮ የሚቆጠር ሆኖ እስከ 5 /አምስት/ ዓመት ባለው ጊዜ ወስጥ ለድርጅቱ የሚያስፈልጉትን የካፒታል ዕቃዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ ይፈቀድለታል፡፡

## አንቀጽ4

## ለቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የሚፈቀዱ የካፒታል ዕቃዎች

1. በዚህ መመሪያ አንቀፅ 3 ለተመለከቱት የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የሚያስፈልጉ የካፒታል ዕቃዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ የሚፈቀደው የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የኮከብ ደረጃ ለሰጣቸው ወይም እንደሚሰጣቸው በደብዳቤ ላረጋገጠላቸው ከዚህ ቀጥሎ ባለው ሠንጠረዥ መሠረት ይሆናል፡፡

## ሠንጠረዥ

## የኮከብ ደረጃ ላላቸው ሆቴሎች /የሪዞርት ሆቴልን ጨምሮ/ ፣ሞቴሎች፣ሎጆች እና ሬስቶራንቶች

## ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የሚፈቀዱ የካፒታል እቃዎች

| ተ.ቁ | የስራ ክፍል | የዕቃው ዓይነት |
|---|---|---|

| | | |
|---|---|---|
| 1 | **የእንግዳ መቀበያ እና ሚፈያ ክፍል** | ➢ ለእንግዳ ሚፈያ የሚሆኑ ወንበሮችና ጠረጴዛዎች<br>➢ አንድ ቴሌቪዥን ከነማስቀመጫው<br>➢ አንድ የገንዘብ ካዝና<br>➢ ለእንግዳ መቀበያ ክፍል ሰራተኞች የሚያገለግሉ የሚስተናገጃ ደስኮች፣ ወንበሮች፣ ጠረጴዛዎች እና ቁምሳ<br>➢ አንድ የማዞሪያ ስልክ ከተጓዳኝ እቃዎቹ ጋር<br>➢ የስልክ ቀፎዎች<br>➢ የሻንጣ፣ የመጽሐት እና የመጽሐፍ ማስቀመጫ እና ማን<br>➢ የእንግዳ ዕቃ ማጓጓዣ<br>➢ የክፍል ወስጥ አየር መቆጣጠሪያ፣ ማፈሻ ማቀዝቀዣና ማሞቂያ መሣሪያ<br>➢ የኤሌክትሮኒክስ የበር መክፈቻ ቁልፍ /ቁልፎች/<br>➢ ምንጣፍ እና መጋረጃዎች ከነአክሰሰሪያቸው /በክፍሉ ልክ/<br>➢ አንድ የፎጣ ማሞቂያ እና ማቀዝቀዣ ማሽን<br>➢ አንድ ዊልቼር<br>➢ አንድ ዶላር ቼከር ማሽን<br>➢ አንድ የፓስፖርት ስካነር ማሽን<br>➢ አንድ የብር መቁጠሪያ ማሽን<br>➢ አንድ የዕቃ መደርደሪያ<br>➢ አንድ ትልቅ መብራት /ሻንደሌየር/<br>➢ ለእንግዳ ሚፈያ ክፍል ከ4 ያልበለጡ ኮምፒውተሮች አንድ ፕሪንተር ያለቢዝነስ ሴንተር አገልግሎት የሚ / |
| 2 | **የመመገቢያ ክፍል** | ➢ የመመገቢያ ክፍል ወንበሮች እና ጠረጴዛዎች<br>➢ የቡና ቤት ወንበሮች፣ ጠረጴዛዎች እና በርጩሞዎች<br>➢ አንድ የወይን ጠጅ ማሻ እና ማቀዝቀዣ<br>➢ የምግብእናየማጠጥማስተናገጃጠረጴዛ፣<br>➢ በግድግዳ ላይ የሚሠራ የዕቃ ማስቀመጫ እና መደርደሪያ<br>➢ ከአምስት ያልበለጡ የምግብና ማጠጥ ማጓጓዣ ጋሪዎች<br>➢ የልጆች ወንበሮች እና ጠረጴዛዎች<br>➢ የክፍል ወስጥ አየር መቆጣጠሪያ፣ ማፈሻ፣ ማቀዝቀዣና ማሞቂያ መሣሪያዎች<br>➢ የማጠጥ አገልግሎት ማስጫ መሣሪያ፤<br>➢ የዳቦ መጥበሻ መሣሪያ |

| | | |
|---|---|---|
| | | ➢ የቡና እና የሻይ ማፍያ መሣሪያ፣<br>➢ የቡና መፍጫ መሣሪያ፣<br>➢ የምግብ መቀላቀያ፣ የፍራፍሬ መጭመቂያ እና የአልኮል ማጠጮች መቀላቀያ መሣሪያዎች<br>➢ የእቃ ማጠቢያ ገንዳ<br>➢ የእጅ ማድረቂያ መሣሪያ<br>➢ የዊስኪ ጠርሙስ ማንጠልጠዮዎች<br>➢ የበረዶ ቅንጣፉች ማስሪያ እና የበረዶ መፍጫ መሣሪያዎች<br>➢ አንድ የዕቃ ማስያ ካቤኔት፣<br>➢ አንድ የፈንድሻ ማፍኪያ መሣሪያ<br>➢ ምንጣፍ/ከወለሉ ጋር የሚገጠቅ ብቻ/<br>➢ መጋረጃዎች ከነአክሰሰሪያቸው /በክፍሉ ልክ/<br>➢ አንድ የኤሌክትሪክ የቡፌ ዲስፕሌይ<br>➢ አንድ ቴሌቪዥን ከነማስቀመጫው<br>➢ አንድ የኮት ማስቀያ<br>➢ አንድ የማጠጦ ጠርሙስ ማንጠልጠዩ<br>➢ የመጸዳጃ ቤት ማስታወት |
| 3 | **የእንግዳ መኝታ እና የመታጠቢያ ክፍል** | ➢ አልጋዎችና ፍራሾች<br>➢ ቁም ሳጥን እና የአልጋ ጎን ኮሞዲኖዎች<br>➢ የልጆች አልጋዎች እና ፍራሾች<br>➢ ምንጣፍ እና መጋረጃዎች ከነአክሰሰሪያቸው/ በመኝታ ክፍል ልክ<br>➢ የመኝታ ክፍል ዕቃዎች የመጻፊያ ጠረጴዛ፣ የአልጋ ጎን የቡና እና የስልክ ማስቀመጫ ጠረጴዛዎች፣ ሶፋዎች፣ ወንበሮች፣ በርጩሞች፣ ቁምሳጥኖች እና ባለማባሊያ<br>የልብስ ማስቀመጫ ኮሞዲኖዎች/ |

| | | |
|---|---|---|
| | | ➢ የመዋቢያ ጠረጴዛዎች እና ማስታወቆች<br>የስልክ ቀፎዎች / የማታጠቢያ ክፍልን ጨምሮ/<br>➢ የእንግዳ ካዝና፣<br>➢ የክፍል ወስጥ አየር መቆጣጠሪያ፣ ማፍረሻ፣ ማቀዝቀዣ እና ማሞቂያ መሣሪያዎች፣<br>➢ መጥሪያ/ደወል/፣<br>➢ የፎጣ ማስቀያ፣<br>➢ የሳሙና ማያዣ፣<br>➢ የመፀዳጃ ወረቀት ማያዣ፣<br>➢ የእሳት አደጋ ጠቋሚና የውኃ መርጫ መሣሪያዎች<br>➢ ጃኩዚ፣ ቴሌፎን ሻወር ከነ ማሉ ዕቃዎች<br>➢ ቴሌቪዥን ከነ ማስቀመጫው<br>➢ መጥፎ ጠረን የሚያስወጣ ፋን<br>➢ ፍሪጅ<br>➢ የሻንጣ ማስቀመጫ<br>➢ የራስጌ መብራቶች<br>➢ የኤሌክትሮኒክስ የበር መክፈቻ ቁልፍ<br>➢ የበር መመልከቻ ሌንስ<br>➢ የቡና እና የሻይ ማሽን<br>➢ የፀጉር ማድረቂያ ማሽን<br>➢ የሙዚቃ ማጫወቻ ስፒከር ስቴሽን<br>➢ የግድግዳ የማንበቢያ የጎን መብራት<br>➢ አላርም ሬዲዮ ባለሰዓት<br>➢ የኮት ማስቀያ<br>➢ መተኮሻ ጠረጴዛ ከነ ካውያው |
| **4** | **የቤት አያያዝ እና የልብስ ንጽህና ማጠጫ ክፍል** | ➢ ከአምስት ያልበለጡ ለቤት አያያዝ የሚያገለግል ጋሪዎች የቤት አያያዝ እና የልብስ ንጽሕና ማስጫ ክፍል /ለሬስቶራንቶች አልተፈቀደም፡ ለሌሎቹ ተፈቅዷል/<br>➢ ከአምስት ያልበለጡ በኤሌክትሪክ የሚሠሩ የወለል ማፀጃ መሣሪያዎች |

| | | |
|---|---|---|
| | | ➢ ከአምስት ያልበለጡ የምንጣፍ ማፅጃ መሣሪያዎች<br>➢ ከአምስት ያልበለጡ እርጥበና ደረቅ ወለል ማፅጃ መሣሪያዎች<br>➢ ከአምስት ያልበለጡ የወለል መወልወያዎች ከመጨመቂያዎቻቸው ጋር<br>➢ ከአምስት ያልበለጡ በኤሌክትሪክ፣ በእንፋሎት ወይም በጋዝ የሚሠሩ የልብስ ማጠቢያ መሣሪያዎች<br>➢ ከአምስት ያልበለጡ በኤሌክትሪክ፣ በእንፋሎት ወይም በጋዝ የሚሠሩ የልብስ ማድረቂያና መተኮሻ መሣሪያዎች<br>➢ የልብስ መተኮሻ ካወያ ከጠረጴዛው ጋር<br>➢ ከአምስት ያልበለጡ የልብስ ውሃ መጭመቂያ መሣሪያዎች<br>➢ ከአምስት ያልበለጡ የቀላል ጨርቃ ጨርቆችና ልብስ ማድረቂያ መሣሪያዎች<br>➢ ከአምስት ያልበለጡ የልብስ ስፌት መሣሪያዎች የክፍል ወስጥ አየር ማፈሻ፣ መቆጣጠሪያ መሣሪያ<br>➢ የእሳት አደጋ መካላከያ መሣሪያ<br>➢ የልብስ ማድርደሪያ ቁምሳጥን<br>➢ የደረቅ እጥበት መሣሪያ<br>➢ የሴራሚክ ማጽጃ መሣሪያ<br>➢ የወለል ማብረቅረቂያ መሣሪያ<br>➢ የላወንደሪ የእንግዳ ልብስ ማለያ መሣሪያ |
| 5 | **የምግብ ማዘጋጃ እና ማከማቻ ክፍል** | ➢ የጋዝ ወይም የኤሌክትሪክ ምድጃዎች<br>➢ በጋዝ ወይም በኤሌክትሪክ ኃይል ግሎ ለምግብ ማብሰያነት የሚያገለግል የብረት ግሪል የተለያዩ ክፍሎች ያሉት የማብሰያመሣሪያ<br>➢ የዳቦ መጥበሻ መሣሪያ<br>➢ የውሃ ማሞቂያ<br>➢ በዝግታ ማብሰያ መሣሪያ<br>➢ የመቁያ መሣሪያ<br>➢ የስጋ መፍጫ እና የሥጋና አጥንት መቁረጫ መሣሪያ<br>➢ የምግብ ቅርፅ ማስጫ መሣሪያ<br>➢ የዳቦ ማጋገሪያ መሣሪያና ትሪዎች |

| | | |
|---|---|---|
| | | ➢ የምግብ ማዘጋጃ ጠረጴዛ<br>➢ የኬክ ማስሪያ መሣሪያ<br>➢ የአይስክሬም ማስሪያ መሳሪያ<br>➢ የምግብ መቀላቀያ/መደባለቂያ መሣሪያ<br>➢ የማእድ ቤት ማሄን<br>➢ የኑድል/ የቀጭን ፓስታ ወይም የላዛኛ ወይም የራቪዮሊ/ ማዘጋጃ መሣሪያ<br>➢ መደበኛ እና/ወይም ግዙፍ ማቀዝቀዣ<br>➢ የዕቃ/የሳህን፣ የብርጭቆ እና/ወይም የስኒያ ማጠቢያ መሣሪያ<br>➢ የእቃ ማጠቢያ ገንዳ/ሲንክ ከተጓዳኝ እቃዎች ጋር<br>➢ ማቀዝቀኘያ ቤት፣<br>➢ የእቃ ማስቀመጫ መደርደሪያዎች<br>➢ የሳሀን ማሞቂያ መሣሪያ፣<br>➢ የምግብ ማዘጋጃ ገበታ፣<br>➢ የክፍል ወስጥ አየር መቆጣጠሪያ፣ ማፍረሻ፣ ማቀዝቀዣ ማሞቂያ መሣሪያዎች<br>➢ የእሳት አደጋ መከላከያ መሣሪያ<br>➢ የጭስ ማውጫ መሣሪያ (Hood)<br>➢ የዳቦ ማኮፈሻ፣ማቡኪያና መዳመጫ መሣሪያ<br>➢ የእንቁላል መቀላቀያ መሣሪያ<br>➢ የምግብ እና የፍራፍሬ መፍጫ መሣሪያ<br>➢ የድንች መጥበሻ መሣሪያ<br>➢ የፒዛ መጋገሪያመሣሪያ<br>➢ የዶሮ መጥበሻ መሣሪያ<br>➢ የምግብማሞቂያመሣሪያ<br>➢ የሾርባ ማሞቂያ መሣሪያ |
| 6 | **የግብዣ እና የማሰብሰቢያ አዳራሽ** | ➢ የስብሰባ ወንበሮችና ጠረጴዛዎች<br>➢ ማጋገሪያ መሳሪያዎች<br>➢ አዶቪዥዋል መሳሪያዎች<br>➢ የድምጽ አቫኩዌሽን ሲስተም<br>➢ የትርጉም ማስተላለፊያ መሳሪያዎች<br>➢ የክፍል ወስጥ አየር መቆጣተሪያ፤ ማፍረሻ ማቀዝቀዣና ማሞቂያ መሳሪያዎች፤<br>➢ አዳራሹ ወስጥ በቋሚነት የሚተከል ፕሮጀክተር<br>➢ አንድ ቴሌቪዥን ከነማስቀመጫው |

| | | |
|---|---|---|
| | | ➢ ምንጣፍ እና ማረጃዎች/በአዳራሹ ልክ/ |
| 7 | **የፊዚዮ-ቴራፒ፤ የስፖርትና የመዝናኛ አገልግሎት ማስጫ ክፍል** | ➢ በቤት ወስጥ ለሚደረጉ ስፖርታዊ ልምምዶች የሚያስፈልጉ የጅምናዚየም መሣሪያዎች<br>➢ የስቲም ባዝ አገልግሎት ማስጫ መሣሪያ<br>➢ የሳወና እና/ወይም የጃኩዚ አገልግሎት ማስጫ መሣሪያ<br>➢ አንድ ቴሌቪዥን ከነ ማስቀመጫው |
| 8 | **የመዋኛ ስፍራ** | ➢ የወሃ ማማጥሜ መሣሪያ፣<br>➢ በመዋኛ ስፍራ ለሚረፊያ የሚገለግሉ ወንበሮች/ማጋለያዎች፣<br>➢ የመዋኛ ወሃ ማጥሪያ መሣሪያ<br>➢ የእንግዳ ዕቃ ማስቀመጫ ሎከር<br>➢ የቁም ሻወሮች |
| 9 | **የወበት ማጠበቂያ ክፍል አገልግሎት** | ➢ የማክጅ አልጋዎች<br>➢ የፎጣ ማሞቂያ ማሽን<br>➢ የክፍል ማሞቂያና ማቀዝቀዣ መሣሪያ<br>➢ የስቲም ባዝ፣ የሳወና እና/ወይም የጃኩዚ አገልግሎት<br>➢ የእንግዳ መቀበያ ወንበሮች እና ጠረጴዛዎች<br>➢ የእንግዳ ልብስ ማስቀመጫ ሎከር |

| | | |
|---|---|---|
| 10 | **ተዛማጅ አገልግሎት** | ➢ ጀነሬተር<br>➢ የወሃ ፓምፕ<br>➢ ለባዮ ጋዝ ማበላያ ግንባታ የሚውሉ የካፒታል ዕቃዎች<br>➢ የእሳት ማጥፊያ መሣሪያዎች<br>➢ የእሳት አደጋ ማስጠንቀቂያ መሣሪያዎች/የእሳት አላርም/<br>➢ የመጀመሪያ ደረጃ የሕክምና ዕርዳታ ማስጫ መሣሪያዎች<br>➢ በማዕከላዊ ቦታ የሚቀመጡ የደህንነት መቆጣጠሪያ መሣሪያዎች እና/ወይም ካሜራዎች ከታጓዳኝ እቃዎች<br>➢ የሰወና የሻንጣ ሚዛተሻ መሣሪያዎች<br>➢ በእጅ የሚያዙ የሰው ሚዛተሻዎች<br>➢ የህንጻ እና የንብረት ሜጅመንት ሲስተም ከነአክሰሰሪው<br>➢ የመኪና ሚዛተሻ ማስታወት<br>➢ የሰራተኛ የጣት አሻራ መቆጣጠሪያ ማሰሪያ<br>➢ የበር ካርድ ሪደር |

## <u>አንቀጽ 5</u>

## <u>ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው የሚገቡ ዕቃዎች ብዛት አወሳሰን</u>

1. ከላይ በሠንጠረዡ የተገለጹት በጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማበረታቻው የሚፈቀዱ የካፒታል ዕቃዎች ማጠን/ብዛት የሚወሰነው፡

1.1. የመኝታና ማታጠቢያ ክፍል ቁሳቁሶችና ዕቃዎች በየክፍሎቹ ኘላንና ብዛት መሠረት ነው፡፡

1.2 ከመኝታና ማታጠቢያ ክፍል ውጭ ላሉት ቁጥራቸው በየዕቃዎቹ ትይዩ ላልተጠቀሱ ሌሎች ቁሳቁሶች በማስተናገድ አቅማቸው /ለምሳሌ ለስብሰባ አዳራሽ የሚያስፈልጉ ወንበሮች በአዳራሹ ዲዛይን በሚይዘው ተሳታፊ ብዛት፣ወዘተ/ መሠረት ይሆናል፡፡

2. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 3 ከተጠቀሱት የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች መካከል በአንድ ወይም ከአንድ በላይ ለሚሠማሩ ማንኛውም ባለሀብት የካፒታል እቃዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ለማስገባት የሚፈቀድለት ባለሀብቱ፡ -

2.1 ሜሬት ስለማግኘቱ ሕንፃ ተከራይቶ ወይም ገንብቶ ከሆነ 80 ከመቶ ግንባታው ማጠናቀቁን/ ሕጋዊ ማስረጃ፣

2.2 ኘሮጀክቱ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ስለመጀመሩ ማለትም የሜሬት ዝግጅት፣ መሠረተ ልማት፣ማጋዘን፣ መንገድ እና የመሳሰሉት ስራዎች እየተከናወኑ ስለመሆናቸው ከፌዴራል ወይም ከክልል የኢንቨስትመንት ማስሪያ ቤት የተሰጠውን ማስረጃ፣

2.3 ለኘሮጀክቱ የሚያስፈልጉ የካፒታል እቃዎች ከውጭ አገር ስለመግዛታቸው ቢልኦፍ ሌዲንግ (Bill of Lading) ወይም ኤርዌይ ቢል (Air Way Bill) ወይም ትራክ ዌይ ቢል(Truck Way Bill ) እና የግዥ ደረሰኝ ( Commercial Invoice) ወይም የካፒታል እቃዎቹ ከሀገር ወስጥ የተገዙ ከሆነ የግዥ ደረሰኝ ከአስፈላጊ ማስረጃዎች ጋር፣

2.4. የካፒታል እቃው በባንክ ብድር የሚገዛ ከሆነ የብድሩ ስምምነት ሠነድ እና/ወይም በራስ

ገንዘብ የሚገዛ ከሆነ ባለሀብቱ በባንክ ሂሳቡ ያለውን የገንዘብ መጠን የሚገልጽ ወቅታዊ የባንክ መግለጫ( Bank Statement)

2.5. የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቱ/ኘሮጀክቱ በደንብ ቁጥር 173/2002 በተደነገገው መሠረት የሚጠበቅበትን የባለኮከብ ደረጃ ማስፈርት ስለማሟላቱ/እንደሚያሟላ የሚገልጽ ከባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የተጻፈ የድጋፍ ደብዳቤ የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብቱን ለሚፈቅደው አካል ሲያቀርብ ብቻ ነው፡፡